በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ፍትህ ቢሮ
የህግ ምክር፣ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

THE AMAHARA NATIONAL REGIONAL STATE
JUSTICE BUREAU
LEGAL COUNSELING, DRAFTING AND COMPILATION
DIRECTORATE

ቁጥር
Ref. No የሀ/ም/ማጠ/ዳ/1021/18
ቀን
Date 23/04/2018 ዓ.ም

ለአብክመ መንገድ፣ ትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ቢሮ

**ባህር ዳር፤**

ጉዳዩ፡ **መመሪያ ምዝገባን ይመለከታል**

በአማራ ክልል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ.ም እንደተደነገገው ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም አዲስ መመሪያ አውጥቶ ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት መመሪያውን ከነማብራሪያው በመላክ እንዲሁም አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበሩ መመሪያዎችን አዋጁ በወጣ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለፍትህ ቢሮው በመላክ እንዲመዘገቡ ማድረግ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡

በዚህ መሰረት መስሪያ ቤቱ በቁጥር ት/ሎ/ባ/08-360/18 በቀን 24/03/2018 በተጻፈ ደብዳቤ የአማራ ክልል መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ የትራንስፖርት አገልግሎት ኢንስፔክሽን ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 009/2011 ምዝገባ እንዲከናወን መላኩ ይታወቃል፡፡

ስለሆነም ፍትህ ቢሮ በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀፅ 1 በተሰጠው ስልጣን መሠረት የተላከለትን መመሪያ ቁጥር 009/2011 ዓ.ም ሕጋዊነቱን፣ መሰረታዊ መብቶችና መርሆችን የማይጥስ መሆኑን መርምሮና አስተካክሎ መመሪያው በክልል ደረጃ መመሪያ ቁጥር 26/2018 ዓ.ም ሆኖ የተመዘገበ ስለሆነ የተመዘገበውን መመሪያ ቅጂ 20 ገጽ በዚህ ሸኚ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ይስማው ዘመነ
የህግ ምክር፣ማርቀቅና ማጠቃለል
ዳይሬክቶሬት ዓቃቢ ህግ

ግልባጭ//

- ለቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት፤ (ያለ አባሪ)
- ለፍት/ሕግ ጉዳ/ዘር/ምክትል ቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት

**ፍትሕ ቢሮ**

Tel.No 058 222 0794/793 ✉ 995 Fax- 0582221530
☎ 058 220 37 57

መመሪያ ቁጥር 26/2018

የአማራ ክልል መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ የትራንስፖርት አገልግሎት ኢንስፔክሽን ማስፈጸሚያ መመሪያ

የአብክመ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ የመንገድና የትራንስፖርት ዘርፍን የሚመራ ተቋም እንደ መሆኑና በትራንስፖርት ዘርፍም አንዱ የሥራ መስክ የአሽከርካሪና ተሽከርካሪን አሠራር በህግ ማዕቀፍ እየተከታተሉ መምራት አስፈላጊ በመሆኑ ፣

በትራንስፖርት ስራ መስክ ለሚደረገዉ እንቅስቃሴ ምቹ ሁኔታዎች መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤ በትራንስፖርት ዘርፍ ህጋዊ ሆኖ የተሠማራዉን የዘርፉን ማህበረሠብ ለመደገፍ፣ በህገ ወጡ ላይ ደግሞ አስፈላጊዉን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

የህብረተሰቡን ህይወት፣ ንብረትና ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥሉ የትራንስፖርት ተሽከርካሪዎችን የቴክኒክ ሁኔታና የአሽከርካሪዎችን የሙያ ስነ-ምግባር እንዲሁም የማሽከርከር ብቃት መጓደል ማስተማርና የዕርምት እርምጃ መዉሰድ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማትን፣ የጥገና ተቋማትን፤ የአሽከርካሪ ማሠልጠኛ ተቋማትን፤ የትራንስፖርት ማህበራትን ህገወጥ እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር እና በቢሮዉ ዳይሬክቶሬቶች የሚሠጡ አገልግሎቶች ከሙስናና ከብልሹ አሠራር የፀዱ እንዲሆኑ ማድረግ ተገቢና ወሳኝ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአብክመ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ በተሻሻለዉ የአብክመ የአስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ ማደራጀትና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 230/2011 አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀፅ 1(ሠ) ድንጋጌ ስር በተሠጠዉ ስልጣን መሠረት በማድረግ ይህን መመሪያ አዉጥቷል፡፡

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ
The ANRS Bureau of Justice
የህግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠናቀቅ ዳይሬክቶሬት

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1.አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ" በአማራ ክልል መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ የትራንስፖርት አገልግሎት ኢንስፔክሽን ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 26/2018 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፤

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፦

1/ "ቢሮ" ማለት የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ነው፤

2/ "መምሪያ" ማለት በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ስር ያሉ የዞን መንገድና ትራንስፖርት መምሪያዎች ማለት ነው፤

3/ "የትራንስፖርት አገልግሎት ክትትልና ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት" ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት በአብክመ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ወደታች በየደረጃዉ በሚገኙ መዋቅሮች የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ግለሰቦችና ተቋማትን አሰራራቸውን በውስጥና በውጭ ኢንስፔክሽን በማረጋገጥ የማስተካከያ እርምጃ የሚወሰድ ዳይሬክተር ፣ ቡድን ወይም ፈፃሚ ማለት ነዉ ፤

4/ "የትራንስፖርት አገልግሎት ክትትልና ኢንስፔክሽን ቡድን" ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት በአብክመ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ስር ባሉ የዞን መንገድና ትራንስፖርት መምሪያዎች ውስጥ ያለ ቡድን መሪ እና በቡድኑ ውስጥ ያሉ ፈፃሚዎችን ያካተተ ነው፤

5/ "መመሪያ" ማለት የክልሉ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ በትራንስፖርት ዘርፍ ከክልል እስከ ወረዳ ድረስ ባለው መዋቅር የሚጠቀምባቸው የአሰራር መመሪያዎች ማለት ነው፤

6/ "ጽ/ቤት" ማለት በሜትሮፖሊታንት ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ጽ/ቤትና የወረዳ የመንገድና ትራንስፖርት ጽ/ቤት ማለት ነው ፤

7/ "ህገወጥ ስምሪት" ማለት በህዝብ ፤ በከተማ ፤ በውሀና በጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት ዙሪያ የወጡ የሕግ ድንጋጌዎችን የሚጥስ /የሚተላለፍ/ ማንኛውም ድርጊት ወይም ስምሪት ነው፤

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ The ANRS Bureau of Justice የህግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠናቀቅ ዳይሬክቶሬት

8/ "ኢንስፔክሽን" ማለት በትራንስፖርት ዘርፍ አገልግሎት የሚሰጥባቸው አዋጆች ፤ደንቦች መመሪያዎችና ስታንዳርዶች በተገቢው መንገድ መተግበራቸውን የሚረጋገጥበት አሰራር ነው፤

9/ "የውስጥ ኢንስፔክሽን" ማለት በመንገድና ትራንስፖርት ቢሮ በትራንስፖርት ዘርፍ ስር የተደራጁትን ዳይሬክቶሬቶች ፣ ቡድኖችና ባለሙያዎች የሚሰጡት የአገልግሎት በተቀመጠው የአሰራር መመሪያ እና ስታንዳርድ መሰረት መሆኑን ኢንስፔክት ማድረግ ማለት ነው፤

10/ "የውጭ ኢንስፔክሽን" ማለት በትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፍ ላይ የተሰማሩ የዘርፉ ተዋናዮች ማለትም የተሽከርካሪ ጥገና ተቋማት ፤ የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት ፣ የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት ፣ የህዝብ፤ የከተማ ፣ የጭነት እና የውሀ ትራንስፖርት ማህበራት ፣ ማንኛውም በመንገድ ላይ የሚንቀሳቀሱ (የቤት ፣ የንግድ ፣ የመንግስትና የድርጅት) ተሽከርካሪዎች እንዲሁም በውሃ ላይ በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀሱ አነስተኛ ፣ መካከለኛና ከፍተኛ ጀልባዎችን በመመሪያው እየሰሩ መሆናቸውን የሚረጋገጥበት አሰራር ማለትነው፤

11/ "ማገድ" ማለት በኢንስፔክሽን ወቅት የተገኙ ጉድለቶችን መነሻ በማድረግ ጉድለቶች እስኪስተካከሉ ድረስ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለተወሰነ ወይም የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ማስቆም ማለት ነው፤

12/ "መደበኛ ኢንስፔክሽን" ማለት ዕቅድና ፕሮግራም ተይዞለት የሚከናወን የኢንስፔክሽን /የምርመራ / ስራነው፤

13/ "ድንገተኛ ኢንስፔክሽን" ማለት ዕቅድና ፕሮግራም ሳይያዝለት በድንገት ወይም መረጃ /ጥቆማ/ ሲደርስ የሚከናወን የኢንስፔክሽን /የምርመራ/ ስራ ነው።

14/ "የተሽከርካሪ ጥገና እና አካል ሥራ ጋራዥ አገልግሎት" ማለት በተሽከርካሪ ላይ የሚታየውን የቴክኒክና የአካል ጉድለት ለማሟላት በየትኛውም የተሽከርካሪ ክፍል ላይ የሚከናወን የጥገና ማስተካከል ሥራ ነው ፤

15/ "የተሽከርካሪ ምርመራ" ማለት አንድ ተሽከርካሪ በመንገድ ላይ የቴክኒክ ብቃትና ምቾት ያለው መሆኑንና የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት የመቻል ብቃቱን ለማረጋገጥ የሚደረግ የቴክኒክ ምርመራ ነው።

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትሕ ቢሮ The ANRS Bureau of Justice የህግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠናቀቅ ዳይሬክቶሬት

16/ "የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋም" ማለት ተሽከርካሪ በማሽከርከር ተግባር ላይ ተሰማርተው ደረጃ የሚያሳድጉና እና ለወደፊት ተሽከርካሪ ለማሽከርካር የእጩ አሽከርካሪዎች የንድፈ ሀሳብና የተግባር ሥልጠና የሚሰጥበት እና እንዲያሰለጥኑ ፈቃድ የተሰጠው ተቋም ነው፤

17/ "የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ" ማለት ባለሞተር ተሽከርካሪዎችን ለመንዳት የሚያስችል በአዋጅ ቁጥር 1074/2010 እና አዋጁን ተከትለው በሚወጡ ደንብ እና መመሪያዎች መሰረት የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

18/ "ማህበር" ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት የህዝብ ፣ የከተማ ፣ የውሀ ትራንስፖርት እና የጭነት ትራንስፖርት፣የማሰልጠኛተቋማት እና የጥገና ተቋማት ዙሪያ አገልግሎት የሚሰጡ ባለንብረቶች ማህበር ማለት ነው፤

19/ "ስምሪት" ማለት የህዝብ ፣ የከተማ ፣ የውሀ እና የጭነት ማመላለሻ ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ብቁ ሆነው በቀረቡ ተሽከርካሪዎች አማካኝነት የሚደረግ ጉዞ ወይም እንቅስቃሴ ማለት ነው፤

20/ "ነፃ ስምሪት" ማለት ኦፕሬተሮች በወሰዱት ፈቃድ መሠረት በሥራ መርሐ ግብር በታገዘ ነፃ በሆነና በጤናማ ውድድር የሚሠሩበት አሠራር ነው።

21/ "ልዩ" ማለት በመደበኛ ሥምሪት መሥመሮችም ሆነ በሌሎች በተጓዙና በአገልግሎት ሰጪው ኦፕሬተር መካከል በሚደረግ ስምምነት የሚሰጥ የትራንስፖርት አገልግሎት ነው፤

22/ "ኦፕሬተር" ማለት የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የአገልግሎቱን ዓይነት በመለየት ፈቃድ ያወጣ የተሽከርካሪ ባለንብረት ሰው ወይም ድርጅት ነው፤

23/ "ውድድር" ማለት በደረጃ አንድ በደረጃ ሁለት ፣ በደረጃ ሶስት መካከል ኦፕሬተሮች በሚሰጡት የአገልግሎት ዓይነት ፣ በክፍያ እና በምቾት መሰረት ተገልጋዩ የራሱን ምርጫ በመወሰን የሚገለገልበት የስምሪት አፈጻጸምና የተሽከርካሪ አቅርቦት ስርዓት ነው፤

24/ "የሥራ መርሃ ግብር" ማለት ኦፕሬተሮች በሚንቀሳቀሱበት መስመር በሚያስከፍሉት ክፍያ ታሪፍ፤ የሚመደቡት የተሽከርካሪዎች ብዛት መነሻና መድረሻ ሰዓትና የሥምሪት መስመሮችን የያዘ የ 15 ቀን ፣ የወር፣ የ 3 ወር ወይም የ6 ወር እንደ አስፈላጊነቱ የዓመትና ከዚያ በላይ በጊዜ የተገደበ የሥራ እንቅስቃሴ ዕቅድ ነው፤

25/ "የማኅበር ፈቃድ" ማለት በማኅበር ተደራጅተው አገልግሎት ለመስጠት ጥያቄ የሚያቀርቡና የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ለወሰዱ ባለሀብቶች የሚሰጥ የማኅበር ምዝገባ ፈቃድ ነው፤

26/ "የሙያ ብቃት ማረጋገጫ" ማለት በፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ወይም በክልል ትራንስፖርት በተዋረድ እስከ ወረዳ ጽ/ቤት ድረስ በተዋቀረው አካል አገልግሎት ጠያቂዎች በጠየቁት የአገልግሎት አይነት ፌደራሉ ወይም ክልሉ ባወጣው ስታንዳርድ መሰረት አሟልቶ አገልግሎቱን እንዲሰጥ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም ድርጅት ነው፤

27/ "ምዝገባ የተደረገለት ተሽከርካሪ" ማለት ተፈላጊ ሰነዶች መሟላታቸው ተረጋግጦ በባለንብረቱ ስም የባለቤትነት ምዝገባ የተደረገለት ተሽከርካሪ ነው፤

28/ "መለያ ቁጥር" ማለት አንድ ተሽከርካሪ ምቹቱ እና የቴክኒክ ብቃቱ በምርመራ ተረጋግጦ አግባብነት ባለው አካል ሲመዘገብ የሚሰጠው የቁጥሮች፣የፊደሎችና የምልክቶች ጣምራ ነው፤

29/ "ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት/ቦሎ" ማለት አንድ ተሽከርካሪ በመንገድ ላይ ለመንቀሳቀስ የቴክኒክ ብቃትና ምቾት ያለው መሆኑ ተረጋግጦ የሚሰጥና ለአንድ አመት የሚፀና ተለጣፊ ምልክት ነው፣

30/ "የመለያ ቁጥር ሠሌዳ" ማለት በፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን የሚታተም ተሽከርካሪውን በመንገድ ላይ በቀላሉ ለመለየት እንዲያስችል በተሽከርካሪው ከፊትና ከኃላ ላይ የሚደረግ መለያ ቁጥር ነው;

31/ "ኦፊሲዮል ሰነዶች" ማለት በአዋጅ ቁጥር 681/2002 መሰረት ባለንብረትነትን በሚገባ ለማሳወቅና የቴክኒክ ምርመራ ለማካሄድ የሚቀርቡ ማመልከቻዎች ፣ የጉምሩክ ሰነዶች፣ የቴክኒክ ምርመራ ቅጾች ፣ ደብዳቤዎችና ሌሎች ጽሁፎች ናቸው፣

32/ "ድንገተኛ የተሽከርካሪ የቴካኒክ ምርመራ" ማለት ተሽከርካሪዎች አመታዊ የተሽከርካሪ የቴካኒክ ምርመራ አድርገው ወይም ሳያደርጉ መስራት አለመስራታቸውን ባልታሰበ ሰዓት በማንኛውም ባለሞተር በተሽከርካሪዎች ላይ የሚደረግ ምርመራ ነው፤

33/ "ግብረ-መልስ" ማለት በኢንስፔክሽን ወቅት የተገኙ ችግሮችን በመለየት የተገኙ ችግሮች እንዲስተካከሉ በዝርዝር የሚሰጥ አስተያየት ነው፣

34/በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለፀው አገላለጽ የሴት ጾታንም ያጠቃልላል፡፡

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

በአብክመ የመንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ከክልል እስከታችኛው መዋቅር ድረስ ባለው የውስጥ አሰራር እና ቢሮውም ሆነ ዞኖች የብቃት ማረጋገጫ በሰጧቸውና ባደራጇቸው የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት፣ የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት፣ የተሽከርካሪ ጥገና ተቋማት፣ የተሽከርካሪ መለዋወጫ አቅራቢዎች፤ የከተማ ፤ የህዝብ ፤ የጭነትና የውሀ ትራንስፖርት ማህበራት እንዲሁም በማንኛውም በባለሞተር ተሽከርካሪ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ በአብክመ የመንገድና ትራንስፖርት ቢሮ የትራንስፖርት ዘርፍ የወጡ አዋጆች ፤ ደንቦችና መመሪያዎች ከክልል እሰከ ወረዳ ድረስ ባለው መዋቅር በተገቢው መንገድ መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ ነው፡፡

# ክፍል ሁለት
# ስለ ተግባርና ሀላፊነት

## 5. የትራንስፖርት አገልግሎት ክትትልና ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት ተግባርና ሀላፊነት

1/ በዞንና በወረዳ ለትራንስፖርት አገልግሎት ክትትልና ኢንስፔክሽን ቡድኖችና ባለሙያዎች ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል የአሰራር ማንዋሎችን ያወርዳል አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

2/ የውስጥ እና የውጭ ኢንስፒክሽን መገምገሚያ ቼክ ሊስቶችን ያዘጋጃል ወደ ዞኖች፤ ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች ያወርዳል፤

3/ ዞኖች ፤ ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች በወረደው ቸክሊስት መሰረት በዘርፉ አገልግሎት ሰጭ የሆኑ ተቋማትን በአግባቡ እየገመገሙ መሆኑን ይከታተላል ይቆጣጠራል፤

4/ የትራንስፖርት ማህበራት አደረጃጀት የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት ተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት የተሽከርካሪ ጥገና ተቋማት ብቃት ማረጋገጫ ሲሰጣቸው በወጡ አዋጆች ፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት አድርገው መደራጀታቸውን ይቆጣጠራል፤

5/ የህዝብ ፣ የከተማ ፤ የውሀ ፤ የጭነት ትራንስፖርት ማህበራት ለአሽከርካሪ ማሰልጠኛ፤ ለተሽከርካሪ ምርመራ፤ የተሽከርካሪ ጥገና ተቋማት ቢሮው ያወረዳቸው የአሰራር



የህግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠናቀቅ ዳይሬክቶሬት Bureau of Justice

መመሪያዎች፣ ስታንዳርዶችና በተቋማቱ ውስጥ በተገቢው ሁኔታ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይቆጣጠራል።

6/ የህዝብ ፣ የከተማ ፤ የውሀ ፤ የጭነት ትራንስፖርት ማህበራት የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት፤ የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት ጥገና ተቋማት እና የመለዋወጫ አቅራቢ ድርጅቶችን የሥራ ሁኔታ ፣ አገልግሎት አሰጣጥና አፈጻጸምን ይገመግማል ፣ ችግሮቹን በመተንተን ለኃላፊ ያቀርባል፣ ግብረ መልስም ይሰጣል፤

7/ የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት ለፈተና የሚያቀርቧቸው እጩ አሽከርካሪዎች የተግባርና የንድፈ ሀሳብ ስልጠናውን በአግባቡ መከታተላቸውን በኢንስፔክሽን በማረጋገጥ ችግር በተገኘበት ተቋም ላይ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወስድ ያደርጋል፤አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

8/ የትራንስፖርት ማህበራት በተፈቀደላቸው የተሽከርካሪ አይነት፤ ደረጃ እንዲሁም የተወሰነላቸውን ቁጥር እና የአደረጃጀት መመሪያውን ጠብቀው መደራጀታቸውን በኢንስፔክሽን ያረጋግጣል፤ እንዲረጋገጥ ለዞን፤ ለወረዳና ለከተማ አስተዳደር የኢንስፔክሽን ባለሙያዎችና ለስራ ቡድኖች ድጋፍ ያደርጋል፤

9/ አገልግሎት ሰጭ የትራንስፖርት ተቋማት ሲደራጁ የነበራቸውን የአደረጃጀት ጥንካሬ እንደያዙ እንዲዘልቁ በየጊዜው ይፈትሻል ሲደራጁ ከነበረው ስታንዳርድ አንድለው ሲገኙ በተቀመጠው የአሰራር መመሪያ መሰረት እርምጃ ይወስዳል ወይም ያስወስዳል፤

10/ የትራንስፖርት ማህበራት ፣ የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት ፤ የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት ፤ የጥገና ተቋማት ሥራ ስኬታማ በሆነ መልኩ እንዲከናወን ይቆጣጠራል፤

11/ በቢሮ ስር በትራንስፖርት ዘርፍ የተደራጁ ዳይሬክቶሬቶች ፤ በዞንና በከተማ አስተዳደር ስር የተደራጁ የስራቡድኖች ፤ ባለሙያዎች የሚሰጡት የሚሰጡት ማነኛውም አገልግሎት በመመሪያው መሰረት መሆኑን በውስጥ እንስፔክሽን ያረጋግጣል፤

12/ የመንገድ ትራፊክ ቁጥጥር ባለሙያዎች እና የመናህሪያ ስምሪት ሰራተኞች በአጥፊ አሽከርካሪዎች ወይም ተሽከርካሪዎች ላይ እርምጃ ለመውሰድ በስማቸው ያወጧቸውን የመክሰሻ ፓዶች /ክስቻርጆች/ በአግባቡ ስራ ላይ የዋሉ መሆኑን እና ክፍያ የፈጸመበት ደረሰኝ በትክክል ስለመወራረሱ በኢንስፔክሽን ያረጋግጣል ጉድለት ከተገኘ በአጥፊው ላይ እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል አፈጻጸሙን ይከታተላል፤



ፍትሕ ቢሮ The ANRS Bureau of Justice የህግ ምክር፣ ማርቀቅ ማጠናቀቅ ዳይሬክቶሬት

13/ ለቁጥጥር አስፈላጊ የሆነው የተሽከርካሪ ማስቆሚያ ታፔላ ለሚመለከታቸው ወይም ለተፈቀደላቸው አካላት ብቻ መሰጠቱንና ስራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤

14/ በመናህሪያ ውስጥ እና በመንገድ ላይ የቁጥጥር ስራው በተቀመጠው የአሰራር መመሪያ መሰረት መፈጸሙን ክትትል ያደርጋል ጥፋተኛ ሆነው በተገኙ አሽከርካሪዎች ላይ እርምጃ በመውሰድ እንዲስተካከል ያደርጋል፡፡ የመንገድ ደህንነት ስራውን ውጤታማ ለማድረግና አደጋን ለመቀነስ ከሌሎች አጋር አካላት በቅንጅት እየተሰራ መሆኑን በኢንስፔክሽን ያረጋግጣል የተገኘውን ግኝት ለሚመለከተው ያሳውቃል፤

15/ በአፈፃፀም ላይ የሚገጥሙ ችግሮችና ውሳኔ የሚሹ ጉዳዮችን ለቢሮ ሀላፊው /ለምክትል ቢሮ ሀላፊ በማቅረብ ውሳኔ እንዲያገኙ ያደርጋል ውሳኔ ሲያገኙ በአግባቡ መፈጸማቸውን ይከታተላል፤

16/ የትራንስፖርት አገልግሎት የኢንስፔክሽን ሥራውን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ በቢሮው ካሉ የሥራ ክፍሎች እና ከቢሮው ውጭ ካሉ የመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ተቋማት ጋር በመተባበር ይሰራል፤

17/ በትራንፖርት ተቋማት አግልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ለባለድርሻ አካላት ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እንዲሰጥ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤

18/ በማንኛውም ባለሞተር ተሽከርካሪዎች ላይ ድንገተኛ የቴክኒክ ምርመራ ያካሂዳል፤ችግር በሚታይባቸው ተሽከርካሪዎችን ላልተወሰነ ጊዜ በማገድ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤

19/ በየጊዜው የቴክኒክ ችግር የተገኘባቸው ተሽከርካሪዎች አመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ያደረጉባቸውን የምርመራ ተቋማት በመለየት ተቋሙን በኢንስፔክት አጣርቶ እርምጃ ይወስዳል ወይም ያስወስዳል፤

20/ በኢንስፔክሽን ከሚገኙ ሪፖርቶች በመነሳት የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በማይወጡ የትራንስፖርት ማህበራት ፤ የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት ፤ የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት ፤ የተሽከርካሪ ጥገና ተቋማት እና የተሽከርካሪ መለዋወጫ ድርጅቶች ላይ መመሪያውን ጠብቆ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል ያስወስዳል፤

21/ በኢንስፔክሽን ከሚገኙ ሪፖርቶች በመነሳት የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በማይወጡ የትራንስፖርት ማህበራት ፤ የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት ፤ የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት ፤ የተሽከርካሪ ጥገና ተቋማት አመራሮችና ቅጥር ሰራተኞች ላይ አስፈላጊውን

አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል እንዲወሰድ ያደርጋል የተወሰደውን እርምጃ በሪፖርት እንዲገለጽ ይከታተላል፤

22/ በተለያየ ጊዜ በተደረጉ የቁጥጥር ስራዎች የተገኙ ጉድለቶች መስተካከላቸውን በመከታተል ችግሩን ባላስተካከሉ አካላት ላይ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ለሚመለከተው ያሳውቃል፤

23/ በቁጥጥር ወቅት በማንኛውም ተቋም እና ተሸከርካሪ ፤ አሽከርካሪ በአደገኛ ሁኔታ የሚገኙና ከፍተኛ ጥፋት መሆኑን በሚያረጋግጥበት ወቅት ቀጣይ ዉሳኔ እስኪያገኝ ድረስ ጊዜያዊ እገዳ ይጥላል፤

24/ በዞን ደረጃ ርምጃ ዕንዲወሰድባቸዉ ከቢሮው የተላለፉ ችግሮችን በዝርዝር በማየት እንዲወስን ያደርጋል፡፡

## 6. የዞን መምሪያዎች፣ የወረዳና የከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት አገልግሎት ክትትልና ኢንስፔክሽን ቡድን /ፈፃሚ/ ተግባርና ሀላፊነት

1/ በወረደው የመገምገሚያ ቼክሊስት መሰረት የውስጥ እና የውጭ የኢንስፒክሽን ስራ ይሰራል፤ ችግር ሲገኝ በተቀመጠው የአሰራር መመሪያ መሰረት እርምጃ ይወስዳል ያስወስዳል፤ የተወሰደውን እርምጃ በሪፖርት በየደረጃው ያሳውቃል፤

2/ የትራንስፖርት ማህበራት አደረጃጀት፣ የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት፣ ተሸከርካሪ ምርመራ ተቋማት እና የተሸከርካሪ ጥገና ተቋማት ብቃት ማረጋገጫ ሲሰጣቸው በወጡ አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች መሰረት አድርገው መደራጀታቸውን ይቆጣጠራል፤

3/ ለትራንስፖርት ማህበራት ለአሽከርካሪና ተሸከርካሪ ተቋማት ቢሮው ያወረዳቸው የአሰራር መመሪያዎች፣ ስታንዳርዶችና በተቋማቱ ውስጥ በተገቢው ሁኔታ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይቆጣጠራል፤

4/ የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት ለፈተና የሚያቀርቧቸው እጩ አሽከርካሪዎች የተግባርና የንድፈ ሀሳብ ስልጠናውን በአግባቡ መከታተላቸውን በኢንስፔክሽን በማረጋገጥ ችግር በተገኘበት ተቋም ላይ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤

5/ የትራንስፖርት ማህበራት በተፈቀደላቸው የተሸከርካሪ አይነት፤ ደረጃ እንዲሁም የተወሰነላቸውን ቁጥር እና የአደረጃጀት መመሪያውን ጠብቀው መደራጀታቸውን በኢንስፔክሽን ያረጋግጣል ችግር ካለ እርምጃ ይወስዳል ያስወሰዳል፤

6/ አገልግሎት ሰጭ የትራንስፖርት ተቋማት ሲደራጁ የነበራቸውን የአደረጃጀት ጥንካሬ እንደያዙ እንዲዘልቁ በየጊዜው ይፈትሻል ሲደራጁ ከነበረው ስታንዳርድ



በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትሕ ቢሮ Bureau of Justice የህግ ምክርና ማርቀቅ ማጠናቀቅ ዳይሬክቶሬት

አንድለው ሲገኙ በተቀመጠው የአሰራር መመሪያ መሰረት እርምጃ ይወስዳል ያስወስዳል፤

7/ የትራንስፖርት ማህበራት፣ የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት ፤ የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት ፤ የጥገና ተቋማት ክትትልና ቁጥጥር ሥራ ስኬታማ በሆነ መልኩ እንዲከናወን ይቆጣጠራል፤

8/ በዞኑ፤ በወረዳ እና በከተማ በትራንስፖርት ዘርፍ የተደራጁ ቡድኖች የሚሰጡትን ፈቃድ ወይም ብቃት የተቋሙን የስራ መመሪያ ጠብቀው መከናወናችን በውስጥ እንስፔክሽን ያረጋግጣል፤

9/ በዞኑ፤ በወረዳ እና በከተማ የሚገኙ የመንገድ ትራፊክ ቁጥጥር ባለሙያዎች እና የመናህሪያ ስምሪት ሰራተኞች በአጥፊ አሽከርካሪዎች ላይ እርምጃ ለመውሰድ በስማቸው ያወጧቸውን የመክሰሻ ፓዶች /ክስ ቻርጆች/ በአግባቡ ስራ ላይ የዋሉ መሆኑን እና ክፍያ የፈጸመበት ደረሰኝ በትክክል ስለመወራረሱ በኢንስፔክሽን ያረጋግጣል ጉድለት ከተገኘ በአጥፊው ላይ እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

10/ ለቁጥጥር አስፈላጊ የሆነው የተሽከርካሪ ማስቆሚያ ታፔላ ለሚመለከታቸው ወይም ለተፈቀደላቸው አካላት ብቻ መሰጠቱንና ስራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤

11/ በዞን በወረዳና በከተማ የመንገድ ደህንነት ስራውን ውጤታማ ለማድረግና አደጋን ለመቀነስ ከሌሎች አጋር አካላት በቅንጅት እየተሰራ መሆኑን በኢንስፔክሽን ያረጋግጣል የተገኘውን ችግር በግብረ-መልስ ለሚመለከተው ያሳውቃል፤

12/ በአፈፃፀም ላይ የሚገጥሙ ችግሮችና ውሳኔ የሚሹ ጉዳዮችን ለመምሪያ ወይም ለጽ/ቤት ሀለፊዎች በማቅረብ ውሳኔ እንዲያገኙ ያደርጋል ውሳኔ ሲያገኙ በአግባቡ መፈጸማቸውን ይከታተላል ለቢሮው ሪፖርት ያደርጋል፤

13/ የኢንስፔክሽን ሥራው የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ በዞኑ፤በወረደ እና በከተማ አስተዳደር ካሉ የሥራ ክፍሎች፣ ከመምሪያውና ከጽ/ቤቶች ውጭ ካሉ የመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ተቋማት ጋር በመተባበር ይሰራል፤

14/ በመናህሪያ ውስጥ እና በመንገድ ላይ የቁጥጥር ስራው በተቀመጠው የአሰራር መመሪያ መሰረት መሆኑን ክትትል ያደርጋል ጥፋተኛ ሆነው በተገኙ አሽከርካሪዎች ላይ እርምጃ በመውሰድ እንዲስተካከል ያደርጋል የተገኘው ችግር እንዲስተካከል ለሚመለከተው ሁሉ ያሳውቃል፤



በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ The Amhara ... Bureau of Justice የህግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠናቀቅ ዳይሬክቶሬት

15/ በማንኛውም ባለሞተር ተሽከርካሪዎች ላይ ድንገተኛ የቴክኒክ ምርመራ ያካሂዳል ፤ችግር በሚታይባቸው ተሽከርካሪዎች ላይ የማስተካከያ ጊዜያዊ እርምጃ ይወስዳል ፤ ዘላቂ ዉሳኔ እንዲሠጥ መምሪያዉ ለቢሮ ወረዳ ለመምሪያ ያሳዉቃል፤

16/ በየጊዜው የቴክኒክ ችግር የተገኘባቸው ተሽከርካሪዎች አመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ያደረጉባቸውን የምርመራ ተቋማት በመለየት ተቋሙን በቁጥጥር አጣርቶ እርምጃ ይወስዳል ያስወስዳል እርምጃ የተወሰደባቸውን የዞን መምሪያው ለቢሮው በሪፖርት ያሳውቃል፤

17/ በኢንስፔክሽን ከሚገኙ ግኝቶች በመነሳት የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በማይወጡ የትራንስፖርት ማህበራት ፤ የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት ፤ የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት ፤ የተሽከርካሪ ጥገና ተቋማት ሰራተኞች ላይ አስፈላጊውን አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ ጥፋቱን በዝርዝር ደረጃዉን ጠብቆ መንገድና ትራንስፖርት መምሪያና ለቢሮ ያሳውቃል፤

18/ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በማይወጡ የትራንስፖርት ማህበራት፤የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት፤ የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት፤ የተሽከርካሪ ጥገና ተቋማት እና የተሽከርካሪ የቦርድ አመራሮችና ቅጥር ሰራተኞች አጥፍተው ከተገኙ እንደጥፋታቸው መጠን እያየ አስፈላጊውን አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ የተገኘውን ችግር በማደራጀት ለዞን መምሪያ ሀላፊው፤በከተማ አስተዳደር ለጽ/ቤት ሀላፊ አደራጅቶ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል የተወሰደውን እርምጃ ለክልሉ የትራንስፖርት አገልግሎት ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬትና ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፤

19/ በቁጥጥር ወቅት በማንኛውም ተቋም እና ተሽከርካሪ፤ አሽከርካሪ በአደገኛ ሁኔታ የሚገኙና ከፍተኛ ጥፋት መሆኑን በሚያረጋግጥበት ወቅት በሚመለከተዉ አካል ቀርቦ ዉሳኔ እስኪያገኝ ድረስ ጊዜያዊ ዕገዳ ይጥላል፤

20/ በወረዳ እና በከተሞች የተገኙ ችግሮችን መረጃ በሚገባ አጣርቶ በዞን እርምጃ ከተወሰደ በኃላ ለክልል ያሳዉቃል፣ እርምጃ ያልተወሰደባቸውን አካላት እየተከታተለ እርምጃ እንዲወሰድና ምላሽ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

# ክፍል ሶስት

## ስለመተባበርና ግዴታዎች

### 7. ከክልል ዳይሬክቶሬቶች የሚጠበቅ መተባበርና ግዴታ

1/ በክልል ደረጃ በትራንስፖርት ዘርፍ የሚሰጡ አገልግሎቶች በተቀመጠው የአሰራር መመሪያ መፈጸምና የዞንና የከተማ ፣ የወረዳ መምሪያዎችና ጽ/ቤቶች ተግባራትን በመመሪያው መሰረት እንዲፈጽሙ መከታተልና መደገፍ፤

2/ ወቅታዊ እና አዳዲስ መመሪያዎች በሚወጡበት ወቅት ለትራንስፖርት አገልግሎት ክትትልና ኢንስፔክሽን ዳይሪክቶሪት ማሳወቅ እንዲሁም ለዞን ፣ለከተማ እና ለወረዳ ተቋማት በመላክ በተገቢው መንገድ መፈጸማቸውን መከታተል፤

3/ በትራንስፖር ዘርፍ አገልግሎት የሚሰጥባቸው ሁሉም ተግባራት በኢንስፔክሽን እንደሚረጋገጡ በመረዳት ለስራው መቃናት አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ፤

4/ በኢንስፔክሽን የሚታዩ መረጃዎችን አደራጅቶ ለኢንስፔክሽን ባለሙያዎች አስፈርሞ መስጠትና ኢንስፔክሽኑ ሲጠናቀቅ ፋይሎች በትክክል ስለመመለሳቸው በማረጋገጥ ፈርሞ መረከብ፤

5/ በኢንስፔክሽን ግኝት መሰረት የሚሰጡ ውሳኔዎችን በማስተካከልና በዳይሬክቶሬቱ በኩል የሚወሰዱ እርምጃዎችን በመውሰድ የተወሰዱ እርምጃዎችን ለቢሮ ሀላፊዎችና ለትራንስፖርት አገልግሎት ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሪት ማሳወቅ፤

6/ የዞን የከተማና የወረዳ የስራ ቡድኖች በየደረጃው ለሚደረጉ የኢንስፔክሽኖች ተባባሪ እንዲሆኑና አስፈላጊውን ሰነድ እንዲቀርቡ ድጋፍና አቅጣጫ መስጠት።

### 8. ከዞንና ከተማ አስተዳደር የስራ ቡድኖች የሚጠበቅ መተባርና ግዴታ

1. በዞን፣በከተማና በወረዳ ደረጃ በትራንስፖርት ዘርፍ የሚሰጡ አገልግሎቶች በተቀመጠው የአሰራር መመሪያ መሰረት መፈጸም፤
2. በትራንስፖርት ዘርፍ አገልግሎት የሚሰጥባቸው ሁሉም ተግባራት በኢንስፔክሽን እንደሚረጋገጡ በመረዳት ለስራው መቃናት ሲባል ለኢንስፔክሽን ቡድን አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ፤
3. በኢንስፔክሽን የሚታዩ መረጃዎችን አደራጅቶ ለኢንስፔክሽን ባለሙያዎች አስፈርሞ መስጠትና ኢንስፔክሽኑ ሲጠናቀቅ ፋይሎች በትክክል ስለመመለሳቸው በማረጋገጥ ፈርሞ መረከብ፤
4. በኢንስፔክሽን ግኝት መሰረት የሚሰጡ ግብረመልሶችን በማሰተካከልና በቡድኑ በኩል የሚወሰዱ እርምጃዎችን በመውሰድ የተወሰዱ እርምጃዎችን ለመምሪያ ሀላፊውና ለትራንስፖርት አገልግሎት ኢንስፔክሽን ቡድን ማሳወቅ፤



The ANRS Bureau of Justice

5. ጠቅታዊ እና አዳዲስ  አዋጆች ደንቦችና መመሪያዎች ከክልሉ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ በሚወርዱበት  ወቅት  ለትራንስፖርት  አገልግሎት  ኢንስፔክሽን  ቡድንና  ለሚመለከታቸው የትራንስፖርት ተቋማት ማሳወቅና በተገቢው መንገድ ለመፈጸም እንዲቻል በጥንቃቂ መረዳት የግልጸኝነት ችግር ሲያጋጥም ከክልል ዳይሬክቶሬት ማብራሪያ በመጠየቅ ፤ ግልጽ ከሆኑ  በኂላ መፈጸም፡፡

## 9. የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት ግዴታዎች

1/ የፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣንና የአብክመ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ በአሽከርካሪ ማሰልጠኛ  ተቋማት  አሰራር  ዙሪያ  ያወጣቸውን  አዋጆች፣  ደንቦች፣  መመሪያዎችና እስታንዳርዶችን  ሳይሸራርፉ በተገቢው መንገድ መፈፀም፣

2/ በውጭ  ኢንስፔክሽን  የሚታዩ  መረጃዎችን  አደራጃቶ  ለኢንስፔክሽን  ባለሙያዎች  ማቅረብ ማስመርመር ኢንስፔክሽኑ ሲጠናቀቅ መረጃዎችን በተገቢው መንገድ አደራጅቶ  ማስቀመጥ

3/ በኢንስፔክሽን ግኝት መሰረት በማሰልጠኛ ተቋሙ አማካኝነት  እርምጃ የሚወሰድባቸው አካላት ካሉ እርምጃ በመውሰድ ለሚመለከተው  ማሳወቅ፣

4/ ልዩ ልዩ ሰነዶችን ሰርዞና ደልዞ ትክክለኛ ለማስመሰል ከሚደረግ ተግባር  እራስን መቆጠብ እጩ ሰልጣኞች የተሰረዘ የተደለዘ የትምህርት ማስረጃ እንዲሁም እድሚያቸው የብቃት ማረጋገጫ ለማውጣት ያልደረሱ ሰልጣኞችን አለመቀበል፣ ቢሮው ባወጣው የክፍያ ታሪፍ ብቻ መጠቀምና ከሰልጣኞች ተጨማሪ ክፍያ መጠየቅ ፊጽሞ የተከለከለ መሆኑን በመረዳት ከዚህ ድርጊት መቆጠብ፣

5/ የተሰጣቸውን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት በወቅቱ አሳድሶ መገኘት፣

6/ በኢንስፔክሽን ወቅት የኢንስፔክሽን ቡድን አባላት ወደ  ተቋሙ ሲመጡ  አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ፣

7/ በኢንስፔክሽን  ወቅት  የሚወሰዱ  አስተዳደራዊና  ህጋዊ  እርምጃዎችንና  የሚሰጡ  ግብረ-መልሶችን  በቅንነት መቀበልና ማስተካከል፡፡

## 10. የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት ግዴታዎች

1/ የፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣንና የአብክመ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ በምርመራ ተቋማት አሰራር ዙሪያ ያወጣቸውን አዋጆች፣ ደንቦች ፤ መመሪያዎችና እስታንዳርዶችን ሳይሸራረፉ በተገቢው መንገድ መፈጸም፣

2/ በውጭ  ኢንስቴክሽን  የሚታዩ  መረጃዎችን  አደራጃቶ  ለኢንስቴክሽን  ባለሙያዎች  ማቅረብ ማስመርመር ኢንስፔክሽኑ ሲጠናቀቅ መረጃዎችን በተገቢው መንገድ አደራጅቶ  ማስቀመጥ፣

3/ በኢንስፔክሽን ግኝት መሰረት በምርመራ ተቋሙ አማካኝነት እርምጃ የሚወሰድባቸው አካላት ካሉ እርምጃ በመውሰድ ለሚመለከተው ማሳወቅ፤

4/ ልዩ ልዩ ሰነዶችን ሰርዞና ደልዞ ትክክለኛ ለማስመሰል ከሚደረግ ተግባር እራስን መቆጠብ ፤ ቢሮው ባወጣው የክፍያ ታሪፍ ብቻ መጠቀምና ተጨማሪ ክፍያ መጠየቅ ፈጽሞ የተከለከለ መሆኑን በመረዳት ከዚህ ድርጊት መቆጠብ፤

5/ የተሰጣቸውን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት በወቅቱ አሳድሶ መገኘት፤

6/ በኢንስፔክሽን ወቅት የኢንስፔክሽን ቡድን አባላት ወደ ተቋሙ ሲመጡ አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ፤

7/ በኢንስፔክሽን ወቅት የሚወሰዱ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃዎችንና የሚሰጡ ግብረ-መልሶችን በቅንነት መቀበልና ማስተካከል፡፡

## 11. የተሽከርካሪ ጥገና ተቋማት ግዴታዎች

1/ የፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣንና የአብክመ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ በጥገና ተቋማት አሰራር ዙሪያ ያወጣቸውን አዋጆች ደንቦች ፤ መመሪያዎችና እስታንዳርዶችን ሳይሸራረፉ በተገቢው መንገድ መፈፀም፤

2/ በውጭ ኢንስፔክሽን የሚታዩ መረጃዎችን አደረጃቶ ለኢንስፔክሽን ባለሙያዎች ማቅረብ ማስመርመር ኢንስፔክሽኑ ሲጠናቀቅ መረጃዎችን በተገቢው መንገድ አደራጅቶ ማስቀመጥ

3/ በኢንስፔክሽን ግኝት መሰረት በጥገና ተቋሙ አማካኝነት እርምጃ የሚወሰድባቸው አካላት ካሉ እርምጃ በመውሰድ ለሚመለከተው ማሳወቅ፤

4/ ልዩ ልዩ ሰነዶችን ሰርዞና ደልዞ ትክክለኛ ለማስመሰል ከሚደረግ ተግባር እራስን መቆጠብ ፤ ቢሮው ባወጣው የክፍያ ታሪፍ ብቻ መጠቀምና ተጨማሪ ክፍያ መጠየቅ ፈጽሞ የተከለከለ መሆኑን በመረዳት ከዚህ ድርጊት መቆጠብ፤

5/ የተሰጣቸውን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት በወቅቱ አሳድሶ መገኘት፤

6/ በኢንስፔክሽን ወቅት የኢንስፔክሽን ቡድን አባላት ወደ ተቋሙ ሲመጡ አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ፤

7/ በኢንስፔክሽን ወቅት የሚወሰዱ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃዎችንና የሚሰጡ ግብረ-መልሶችን በቅንነት መቀበልና ማስተካከል፡፡

12. የህዝብና የከተማ ትራንስፖርት ማህበራት ግዴታዎች

1/ የፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣንና የአብክመ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ በማህበራት አደረጃጀት በህዝብና የከተማ ትራንስፖርት በስምሪት አሰጣጥ ዙሪያ ያወጣቸውን አዋጆች ደንቦች ፣ መመሪያዎችና እስታንዳርዶችን ሳይሸራረፉ በተገቢው መንገድ መፈጸም፤

2/ በውጭ ኢንስፔክሽን የሚታዩ መረጃዎችን አደራጅቶ ለኢንስፔክሽን ባለሙያዎች ማቅረብ ማስመርመር ኢንስፔክሽኑ ሲጠናቀቅ መረጃዎችን በተገቢው መንገድ አደራጅቶ ማስቀመጥ፤

3/ በኢንስፔክሽን ግኝት መሰረት በማህበሩ አማካኝነት እርምጃ የሚወሰድባቸው አካላት ካሉ እርምጃ በመውሰድ ለሚመለከተው ማሳወቅ፤

4/ ልዩ ልዩ ሰነዶችን ሰርዞና ደልዞ ትክክለኛ ለማስመሰል ከሚደረግ ተግባር እራስን መቆጠብ ኦፕሬተሮች/ የተሽከርካሪ ባለሀብቶች/ የተሰረዘ ተደለዘ የኦፕሬተር ፈቃድ ማስረጃ እናሌሎች ማስረጃዎችን ሲያመጡ አለመቀበል፤

5/ በማህበሩ ስር የተደራጁ የተሽከርከሪ ባለሀብቶች ቢሮው ባወጣው ወቅታዊ ታሪፍ ብቻ እንዲጠቀሙ ማድረግ ተጨማሪ ክፍያ መጠየቅ ፈጽሞ የተከለከለ መሆኑን በመረዳት የተሽከርካሪ ባለሀብቶች ከዚህ ድርጊት እንዲቆጠቡ በየጊዜው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን መስራት፤

6/ የተሰጣቸውን የማህበር ኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት በወቅቱ አሳድሶ መገኘትና ባለሀብቶች በማህበር ሲደራጁም ሆነ መርሀግብር ሲያጸድቁ በታደሰ ኦፐሬተር ፈቃድ ብቻ መሰረት እንዲገለገሉ ማድረግ ፤

7/ በኢንስፔክሽን ወቅት የኢንስፔክሽን ቡድን አባላት ወደ መህበራት ቢሮ ሲመጡ አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ፤

8/ በኢንስፔክሽን ወቅት የሚወሰዱ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃዎችንና የሚሰጡ ግብረ መልሶችን በቅንነት መቀበልና ማስተካከል፡፡

## ክፍል አራት

### የቅሬታ አቀራረብ ስርዓት

11.1 ከመንግስት ሰራተኛ ዉጭ ባለዉ ተቋማት ስለተወሰደዉ እርምጃ በወረዳ ላይ ቅሬታ ያቀረበ ማንኛዉም ተገልጋይ በኢንስፔክሽን ወቅት ሆን ተብሎ ወይም በስህተት ችግር ተፈጥሮብኛል ካለ በመጀመሪያ ለወረደዉ /ለከተማዉ/ ፅ/ቤት ኃላፊ ያቀርባል ፣ ፅ/ቤት ኃላፊዉ ከወሰነበት ይግባኝ ለትራንስፖርት መምሪያ ይቀርባል ዞን መምሪያዉ አይቶ ከወሰነበት ዉሳኔዉን ካፀናዉ ለክልል ያቀርባል፡፡ የክልሉ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ዉሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

11.2 ለወረዳዉ/ ለከተማዉ ፅ/ቤት ሃላፊ የሚቀርበዉ ቅሬታ የኢንስፔክሽን ጉድለቱ በተገኘ በ5 ቀን ጊዜ ዉስጥ መቅረብ አለበት ፤የወረዳዉ /የከተማዉ/ ፅ/ቤት ኃላፊ በ10 ቀን ጊዜ ዉስጥ ለቀረበዉ ቅሬታ ምላሽ መስጠት አለበት ፡፡

11.3 ለዞኑ መንገድና ትራንስፖርት መምሪያ በይግባኝ የሚቀርብዉ ቅሬታ የወረዳዉ /የከተማዉ/ ፅ/ቤት ሃላፊ ዉሳኔዉን ባሳወቀ 10 ቀን ጊዜ ዉስጥ መቅረብ አለበት፤ መምሪያዉም የይግባኝቅሬታዉ በቀረበለት በ7 ቀን ጊዜ ዉስጥ ምላሽ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

11.4 የይግባኝ አቤቱታ ለክልሉ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ የሚቀርበዉ መምሪያዉ ለቀረበዉ ቅሬታ ምላሽ በሰጠ 15 ቀን ጊዜ ዉስጥ መሆን አለበት፤ክልሉም በ15 ቀን ጊዜ ዉስጥ ምላሽ መስጠት አለበት ፡፡ ቢሮው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት

### 12. ስለእርምጃ ስለመዉሰድ

#### በክልሉ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ደረጃ እርምጃ የሚወሰድባቸው

12.1 ከመንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ከዞን መንገድና ትራንስፖርት መምሪያዎች እንዲሁም ከከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ጽ/ቤትና ከወረዳ መንገድና ትራንስፖርት ጽ/ቤት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጣቸው አካላት በተለያየ ጊዜ በሚደረግ ኢንስፔክሽን አዋጆችን ፤ ደንቦችንና የአፈጻጸም መመሪያዎችን በመጣስ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ

የማሰረዝ እና ማህበር የማፍረስ ደረጃ ላይ የሚደርስ የዲስፒሊን ግድፈት ፈጽመው ሲገኙ የተገኘውን ችግር በሚገባ ከመረመረ በኋላ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ የተሰጠውን የብቃት ማረጋገጫ ወይም የማህበር ፈቃድ ይሰርዛል፡፡

12.2 ከዞን መንገድና ትራንስፖርት መምሪያዎች እንዲሁም ከከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ጽ/ቤትና ከትራንስፖርት አገልግሎት ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሪት አቅም በላይ ለሆኑ ችግሮች እንዳስፈላጊነቱ ጣልቃ በመግባት ሊያግድ ይችላል ፡፡

## 12.2 በክልል ትራንስፖርት አገልግሎት ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሪት የሚወሰድ እርምጃ

12.2.1 ከመንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ከዞን መንገድና ትራንስፖርት መምሪያዎች እንዲሁም ከከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ጽ/ቤትና ከወረዳ መንገድና ትራንስፖርት ጽ/ቤት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጣቸው አካላት በተለያየ ጊዜ በሚደረግ ኢንስፔክሽን አዋጆችን ፤ ደንቦችንና የአፈጻጸም መመሪያዎችን በመጣስ በህገ ወጥ መንገድ አገልግሎት ሲሰጡ ከተገኙና በኢንስፔክሽን ሲረጋገጥ ከመጀመሪያ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እስከ መጨረሻ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፡፡

12.2.2 የተፈጸመው የዲስፕሊን ግድፈት ከአሰራር መመሪያው አንጻር ሊያሳግድ የሚችል መሆኑ በክልል ኢንስፔክሽን ቡድን ሲረጋገጥ በሁሉም ዞን ሚገኙ የትራንስፖርት ተቋማት ላይ እስከ አንድ ወርና እስከ አንድ ዙር ስልጠና ድረስ ከማንኛውም አገልግሎት በማገድ የተገኘውን ችግር እንዲስተካከሉ ያደርጋል፡፡

12.2.3 እገዳ የተጣለባቸው አካላት ያለባቸው ችግር ማስተካከል ከቻሉ በድጋሚ በኢንስፔክሽን የነበረው ችግር መስተካከሉ ሲረጋገጥ የተጣለውን እገዳ በማንሳት ለዞን መንገድና ትራንስፖርት መምሪያ ያሳውቃል ፡፡

12.2.4 እገዳ የተጣለባቸው የተለያዩ አካላት በተሰጣቸው ጊዜ በእገዳ ውስጥ እያሉ ያለባቸውን ችግር ማስተካከል ካልቻሉ ቀጣይ እርምጃ እንዲወሰድ ወይም የተሰጣቸው የብቃት ማረጋገጫ እነዲሰረዝ ለማድረግ እገዳው ሳይነሳ መረጃውን በማደራጀትከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለክልሉ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ያቀርባል፡፡

## 12.3 በዞን መን/ትራ/መምሪያና በሜትሮ ፖሊታንት ከተሞች ትራ/ጽ/ቤት ደረጃ የሚወሰድ እርምጃ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ The ANRS Bureau of Justice የህግ ምክር ማጠናቀቅ ዳይሬክቶሬት

12.3.1 በዞን መንገድና ትራንስፖርት መምሪያዎች በዞኑ ስር በሚገኙ ከከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ጽ/ቤትና ከወረዳ መንገድና ትራንስፖርት ጽ/ቤት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጣቸው አካላት በተለያየ ጊዜ በሚደረግ ኢንስፔክሽን አዋጆችን ፣ ደንቦችንና የአፈጻጸም መመሪያዎችን በመጣስ በህገ ወጥ መንገድ አገልግሎት ሲሰጡ የተገኙ መሆኑን የኢንስፔክሽን ሪፖርት ሲቀርብለት በመመሪያው መሰረት ከማንኛውም አገልግሎት ያግዳል ለክልል መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ያሳውቃል ሆኖም ግን እገዳ የተጣለባቸው አካላት ያለባቸው ችግር ማስተካከል ከቻሉ በድጋሚ በኢንስፔክሽን ሲረጋገጥ የተጣለውን እገዳ ያነሳል ::

12.3.2 እገዳ የተጣለባቸው የተለያዩ አካላት በተሰጣቸው ጊዜ በእገዳ ውስጥ እያሉ ያለባቸውን ችግር ማስተካከል ካልቻሉ ቀጣይ እርምጃ እንዲወሰድ ወይም የተሰጣቸው የብቃት ማረጋገጫ እንዲሰረዝ ለማድረግ እገዳው ሳይነሳ መረጃውን በማደራጀት ለክልሉ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ይልካል፡፡

## 12.4 <u>በዞን/በከተማ አስተዳደር/ ኢንስፔክሽ ቡድን እርምጃ የሚወሰድባቸው</u>

12.4.1 በዞን መንገድና ትራንስፖርት መምሪያና በዞኑ ስር በሚገኙ ከከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት የስራ ቡድን ከወረዳ መንገድና ትራንስፖርት ጽ/ቤት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጣቸው አካላት በተለያየ ጊዜ በሚደረግ ኢንስፔክሽን አዋጆችን ፣ ደንቦችንና የአፈጻጸም መመሪያዎችን በመጣስ በህገ ወጥ መንገድ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑ በኢንስፔክሽን ሲረጋገጥ ከመጀመሪያ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እስከ መጨረሻ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል እርምጃ የተወሰደባቸውን አካላት ለክልሉ የትራንስፖርት አገልግሎት ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት በዝርዝር ያሳውቃል፡፡

12.4.2 የተፈጸመው የዲስፕሊን ግድፈት ከአሰራር መመሪያው አንጻር ሊያሳግድ የሚችል ሆኖ ከተገኘ የተገኘውን የኢንስፔክሽን ውጤት ለዞን መምሪያ ሀላፊው አደራጅቶ በማቅረብ በዞኑ መንገድና ትራንስፖርት መምሪያ አማካኝነት እንዲታገዱ ያደርጋል አፈጻጸሙን ይከታተላል ::

## በትራንስፖርት ዘረፍ በስራላይ ካሉት አፈጻጸም መመሪያዎች ተጨማሪ ተካተው የሚታዩ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | 1. የብቃት ማረጋገጫ ለማዉጣት የሚመጡ ሰልጣኞችን ዕድሜያቸዉ ያልደረሰና ፎርጅድ ማስረጃ ሲያቀርቡ ተቀብሎ የመዘገበ፣ | 1. ለመጀመሪ ጊዜ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ሰልጣኞችን የከፈሉትን ገንዘብ ማስመለስ | የትራ/ አገ/ክት/ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት/ቡድን/ |
| | | 2. ለሁለተኛ ጊዜ ለ1 ዙር ለስልጠና በማገድ የሠልጣኞችን ገንዘብ ማስመለስ | የትራ/ አገ/ክት/ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት |
| | | 3. የተቋሙን የብቃት ማረጋገጫ ለ6 ወር ማገድ | በመምሪያው ወይም በበሮው |
| | | 2. የተቋሙን ብቃት ማረጋገጫ መሠረዝ | ቢሮዉ |
| 2 | 1. በተቋሙ ስም ባልተመዘገበ ተሽከርካሪ ስልጠና መስጠት ፎርጅድ ቦሎ ለጥፎ የተገኘ | 1. የመጀመሪያ ተቋሙን ለ6 ወር ማገድ | በመምሪያው ወይም በበሮው |
| | 2. በፎርጅድ የትምህርት ማስረጃ የተግባርም ሆነ የንድፈሀሳብ አሰልጣኝ ቀጥሮ ሲያሰለጥን የተገኘ | 1. በመጀመሪያ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ | የትራ/ አገ/ክት/ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት/ቡድን/ |
| | | 2. ለሁለተኛ ጊዜ ለሁለት ዙር ከስልጠና ማገድ | በመምሪያው ወይም በበሮው |
| | | 3. ለሶስተኛ ጊዜ ለስድስት ወር ተቋሙን ማገድ | ቢሮው |
| | | 2. ለአራተኛ ጊዜ የብቃት ማረጋገጫን መሠረዝ | ቢሮዉ |
| 3 | 1. በተቋሙ ስም ባልተመዘገበ ተሽከርካሪ ስልጠና መስጠትና የተቋሙ ለማስመሰል በተጭበረበረ ሠነድ የባለቤትነት ሊብሪ በተቋሙ ስም አሰርቶ በመረጃነት ከፋይል ጋር ተያይዞ የብቃት ማረጋገጫ ወስዶበት ከተገኘ | 1. የተቋሙን የብቃት ማረጋገጫ መሰረዝና በህግ እንዲጠየቅ ማድረግ፣ | ቢሮዉ |

## 15. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

በዚህ መመሪያ የተካተቱ የቅጣት አፈጻጸሞች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ መመሪያ ውስጥ ያልተካተቱ እና ከዚህ ቀደም በፌድራል ትራንስፖርት ባለስልጣንም ሆነ በአማራ ክልል መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ በተለያየ ጊዜ የወጡ ቢሮዉ የሚጠቀምባቸዉ የተለያዩ አዋጆች ፣ ደንቦችና ዲሲፕሊን የአፈጻጸም መመሪያዎችን የትራንስፖርት አገልግሎት ክትትልና ኢንስፔክሽን እንደ አንድ የማስፈጸሚያ መመሪያ አድርጎ ይጠቀምባቸዋል፤

## 16. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸዉ ህጎች፣

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛዉም መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ መመሪያ ዉስጥ በተካተቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረዉም ፡፡

## 17. መመሪያዉ የሚፀናበት ጊዜ

1/ ይህ መመሪያ በአብክመ የመንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊ ተፈርሞ ከወጣበት ከየካቲት 14/ 2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው ቢኖርም ይህ መመሪያ በፍትሕ ቢሮ ከተመዘገበበትና አዲስ ቁጥር ከተሰጠበት ቀን በኃላ ተፈጻሚነት የሚኖረው በአማራ ክልል መንገድ፣ ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ቢሮ ድረ ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

የአማራ ክልል መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ

ባህር ዳር